# ዓባይ ደረቀ አሉ !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ዓባይ ደረቀ አሉ የወንዞች አባት ፤
የፍጡራን ዕንባ ሲጎርፍ በማየት ፤
አለበት ኩነኔ በሰራው ሃጢያት ፤
ወገን እየጠማው እንደማጠጣት ፤
ግፍ እንዳላየና እንዳልሰማ ጩኸት ፤
ሲፈስ ከረመና በባዕዳን መሬት ፤
አሁን ደረቀ አሉ ድንጋዩ ፈጠጠ ፤
ከሱ ጅረት ይልቅ የዕንባ ጎርፍ በለጠ ።
አባል ብሎ መጽዋች አባል ብሎ ደግ ፤
በባዕዳን መሬት ሲወርድ ሲያረገርግ ፤
ሲያርስ ሲያርከፈክፍ ሲያለማ መሬት ፤
ሲያበላ ሲያጠጣ ምድረ ጎረቤት ፤
ሲያድል ለሙን መሬት በየደረሰበት ፤
አሁን ቢበዛበት የዜጎች ጩኸት ፤
ዓባይ ደረቀ አሉ የወንዞች አባት ።
ዳግም ላይታለብ ላይሰጥ ወተቱን ፤
ጣናን አመከነ አሟጠጠ ምንጩን ፤
እኔ ድርቅ ልበል እኔ ልሙትልሽ !
ብሎ ዓባይ ደረቀ ጦቢያ ለልጆችሽ !!
እንደ ፈሪ ሌባ ጨለማ አርጎ ተገን ፤
ደቻንቱ ሲነጥቅ ብዙ ድሃ ወገን ፤
አዋሽና ኦሞ ጨክነው በወገን ፤
ጠራርገው ሲወስዱ እንስሳና ሰውን ፤
ዓባይ አከበረ ቃል ኪዳን አደሰ ፤
ዕንባውን ዋጥ አርጎ በልቡ አለቀሰ ።
ምንጩን አደረቀ በጎርፍ ላይወሰድ ማለ ፤
ቆርበ ውሎ ገባ ዓባይ ጦሙን ዋለ ፤
ጾም ጸሎት መረጠ ከሱባኤ ገባ ፤
አይታጠብ ብሎ ወገናችን በዕንባ ።
እኔ ድርቅ ልበል እኔ ልሙትልሽ !
ብሎ ዓባይ ደረቀ ጦቢያ ለልጆችሽ !!

መስከረም 1 ቀን 1999 ዓም ። (september 11 2006)

በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖቼ መታሰቢያ ትሁንልኝ ።

አዲሱ ዓመት ሐዘን ፣ ለቅሶ ፣ ስደት ፣ ወከባና እስራት ተወግደው የተስፋ ብርሃን ጮራ የሚፈነጥቅበት ፤
ሕዝባችን የድል ችቦውን እጅ ለእጅ ተያይዞ በማንበግበግ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራችንን ከፍ አድርጎ የሚያውለበልብበት የፍስሐ ዘመን ይሁንልን ።